# WNYCOSH የሰራተኞች ማእከል

# መብቶችዎን ይወቁ

## ዝቅተኛ ደመወዝ

**$15.00/ሰአት**

የእርሻ ሰራተኞች ዝቅተኛው ደመወዝ $15.00/ሰአት ሲሆን፣ ደመወዙ እንዴት እንደሚገኝ እና የስራ ሁኔታዎችን የሚወስን “የእርሻ ስራ ስምምነት” መደረግ ይኖርበታል

## የዝቅተኛ ደመወዝ የጊዜ ሰሌዳ*

| አመት | ዝቅተኛ ደመወዝ/ሰአት |
|---|---|
| 2024 | $15.00 |
| 2025 | $15.75 |

*ከኒውዮርክ ከተማ ውጪ

## ጉርሻ የሚከፈላቸው ሰራተኞች

- $12.50/ሰአት ደመወዝ ቢያንስ ከ $2.50 ጉርሻ ጋር ወይንም በአሰሪው የሚከፈል
- ደመወዝ ዝቅተኛ ሲሆን የሚገኘው ወይንም በአሰሪው የሚከፈለው የጉርሻ መጠን ይጨምራል
- ጉርሻ የሚከፈላቸው ሰራተኞች በተጨማሪ የስራ ሰአት ሕጎች ሽፋን ያገኛሉ
- ጉርሻ የሚያገኙ ሰራተኞች በአሰሪያቸውም ይሁን በአሰሪያቸው ተወካይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ **ስለ ጉርሻ ክፍያቸው መጠየቅ የለባቸውም**

## የጊዝያዊ ሰራተኞች መብቶች

ጊዝያዊ ሰራተኞች የሚከተሉት መብቶች አሉዋቸው:

- **ከሁለቱም** ማለትም የሚጠቀሙበት ኤጀንሲ እና የአሰሪው አድልዎ ሰለባ ያለመሆን መብት
- ከቋሚ ሰራተኞች እኩል ወይም ተመሳሳይ የደህንነት ስልጠና የማግኘት መብት
- ዝቅተኛው የደመወዝ መጠን

## ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የስራ ቦታ የማግኘት መብት

በዩ.ኤስ. የጤና እና ደህንነት ሕጎች ስር የሚከተሉት መብቶች አለዎት:

- በሚገባዎ ቋንቋ ስልጠና የመውሰድ መብት
- ከሚታወቁ ጎጂ ነገሮች ነጻ የሆነ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ ቦታ የማግኘት መብት
- የጤና እና ደህንነት ችግሮችን ለተቆጣጣሪዎ የማሳወቅ መብት
- ደህንነታቸው ያልተጠበቀ ወይንም ጤናማ ያልሆኑ ሁኔታዎችን በተመለከተ ወደ OSHA ቅሬታ የማስገባት መብት
- ወድያውኑ አደጋ ላይ ሊጥልዎ የሚችል ስራ እንዲሰሩ ሲጠየቁ የመቃወም ወይም እምቢ የማለት መብት
- በስራ ቦታዎ ያሉ ጎጂ ነገሮችን የማወቅ መብት
- ደህንነትን አደጋ ውስጥ ሊከቱ የሚችሉ ነገሮች (የመረጃ ሰጪዎች ጥበቃ) በማሳወቅዎ ምክንያት ለአድልዎ (መባረር፣ መጥፎ ስራ ላይ መመደብ፣ ወዘተ) ያለመጋለጥ መብት
- የሕክምና ምርመራዎች እንዲሁም በስራ አካባቢዎ ላይ ጎጂ ነገሮችን በተመለከተ የተደረጉ ቀጥጥራዊ ምርመራዎችን የማግኘት መብት
- በስራ ቦታዎ ላይ የሚከሰቱ ጉዳቶች እና በሽታዎች የሚመለከት መረጃ የማግኘት መብት

Amharic

## የተጨማሪ ሰአት ስራ

አብዛኞቹ ሰራተኞች በሳምንት ውስጥ ከ 40 ሰአት በላይ ለሰሩዋቸውስራዎች ሁሉ ከመደበኛ ክፍያቸው በ1 ½ የተባዛ ክፍያ የመቀበል መብት አላቸው

ለሚከተሉት ግን ከተጨማሪ ሰአት ስራ ጋር ተያይዞ ልዩ ሁኔታዎች አሉ:

- የእርሻ ሰራተኞች
- አስፈጻሚ ሰራተኞች: ሰራተኞችን መቆጣጠር/ማባረር የሚችሉ እና የሁለት ወይንም ከሁለት በላይ ሰራተኞች ስራን በቀጣይነት የሚቆጣጠሩ
- የሙያ ሰራተኞች: የ 4-አመት ዲግሪ ያላቸው ወይንም የፈጠራ ስራ የሚሰሩ
- አስተዳደራዊ ሰራተኞች: በነጻነት ውሳኔ የመወሰን ስልጣን የተሰጣቸው ወይንም በቀጥታ ከአስተዳደራዊ ፖሊሲዎች ጋር የተያያዙ የጽሕፈት-ቤት/ከፖልበት ስራ የራቁ ስራዎችን የሚሰሩ

## ክፍያ በየስንት ጊዜው ይከፈላል

አብዛኞቹ ሰራተኞች ክፍያዎቻቸውን በ 7 ቀናቶች ውስጥ ማግኘት አለባቸው

## ከአድልዎ ነጻ የመሆን መብት

አርእስት VII እና የኒውዮርክ ስቴት ሰብአዊ መብቶች ክፍል ሰራተኞች ላይ አድልዎ እንዳይፈጸም ይከላከላሉ።

## የአድልዎ ሰለባ እንዳይሆኑ ጥበቃ የሚደረግላቸው ቡድኖች

- ዘር
- የቆዳ ቀለም
- ብሔር
- ሀይማኖት
- ጾታ
- የአካል/አእምሮ ጉዳት
- ጾታዊ ባህሪ
- ወታደራዊ ሁኔታ
- ከዘር ለሚወረስ በሽታ የመጋለጥ እድል
- የቤተሰብ ሁኔታ
- የትዳር ሁኔታ
- የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባ ሁኔታ
- እርግዝና
- ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች (ከስራ ውጪ)
- የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች (ከስራ ውጪ)
- የማህበር አባልነት

## የመረጃ ሰጪዎች ጥበቃ

ሰራተኛ ወደ የመንግስት ኤጀንሲ ቅሬታ ወይንም አቤቱታ በማስገባቱ መቅጣት ወይንም ማባረር ህገወጥ ነው

ማንኛውም አሰሪ አሰሪውን በተመለከተ በቅንነት ወደ መንግስት ኤጀንሲ ቅሬታ ያቀረቡ ሰራተኞችን **መቅጣት አይችልም**

አሰሪ የሚከተሉትን ከፈጸመ ሊወቀስ እና እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል:

- ማባረር/ከስራ ማስወጣት
- ጥቁር መዝገብ ላይ ማስፈር
- የስራ ደረጃን ዝቅ ማድረግ
- የተጨማሪ ጊዜ ስራ/እድገት መከልከል
- አለመቅጠር/ዳግም አለመቅጠር
- ማስፈራራት
- ስጋት ውስጥ መክተት
- ክፍያ መቀነስ
- ሰአት መቀነስ
- የዲሲፕሊን ቅጣት መቅጣት
- ጥቅማጥቅሞችን መከልከል
- የስራ እድገት እድል የሚያቀጭጭ ዳግመ-ምደባ ማካሄድ

## የሰራተኞች ካሳ የማግኘት መብት

### በስራ ላይ ጉዳት ከደረሰብዎ:

- “ደፋ ባልሆነ አካሄድ" ወይንም “በሚስጢር” ካሳ የተቀበሉ ቢሆንም እንኳ የሰራተኞች ካሳ መድህን ተጠቃሚ የመሆን መብት አለዎት
- በአሰሪዎ አማካኝነት የሰራተኛ ካሳ መጠየቂያ ወይንም C-3 ቅጽ መሙላት አለብዎ ወይንም ከWNYCOSH የሰራተኞች ማእከል አስቸኳይ የመረጃ መስመር እገዛ መጠየቅ ይችላሉ **(716) 206-3550**